# ለMedicaid አባላት በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የፌዴራል የማኅበረሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታ ምንድነው፣ የMedicaid አባላት ላይ ምን ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በጀመረ ጊዜ የፌዴራሉ መንግስት የማኅበረሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታ አውጇል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ የግዛት ኤጀንሲዎች ለሁሉም የሕክምና እገዛ ፕሮግራሞች፣ ብቁነታቸው ያበቃ ሰዎችንም ጭምር አካትተው፣ የጤና ክብካቤ ሽፋናቸውን ቀጥለዋል።**

## መደበኛ የMedicaid ሂደቶች የሚጀምሩት መቼ ነው?

- ግዛቶች የMedicaid አባላት አሁንም ለሽፋን ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ 12 ወራት ይኖራቸዋል። ይህ ሂሰት መች እንደሚጀመር ገና አላወቅንም። አባሎቻችንን ወቅትቅዊ መረጃ ከመጠየቃችን በፊት ለአባሎቻችን ሽፋንን አንሰርዝም ወይም አንቀንስም።

## አባላት ሽፋናቸውን ቢያጡስ?

ሁሉም መስፈርቱን የሚያሟሉ የቨርጂኒያ ነዋሪዎች ሽፋን እንዲያገኙ እና ሽፋናቸውን ይዘው እንዲቆዩ እንፈልጋለን። አንድ አባል ከቨርጂኒያ Medicaid ሽፋን ለማግኘት መስፈርቶቹን ማሟላቱ የቀረ ከሆነ፣ የሚከተሉትን ያገኛሉ፡-

- የMedicaid ሽፋናቸው መቼ እንደሚያበቃ ማሳወቂያ፣
- ውሳኔያችን ስህተት እንደሆነ ካሰቡ እንዴት ይግባኝ መጠየቅ እንደሚችሉ መረጃ፣ **እና**
- ወደ Federal Marketplace ሪፈራል እና ሌሎች የጤና ክብካቤ ሽፋኖችን እንዴት መግዛት እንደሚችሉ መረጃ

## አባላት አሁን ምን ማድረግ ይችላሉ?

አባላት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- ለCover Virginia በስልክ ቁጥር 1-855-242-8282 በመደወል ወይም በመስመር ላይ commonhelp.virginia.govን በመጎብኘት መገኛ መረጃቸውን ወቅታዊ ማድረግ። አባላት አስፈላጊ ማሳወቂያዎችን እንዲቀበሉ እና ተጨማሪ መረጃ በምንፈልግ ጊዜ ማግኘት እንደንችል፣ በፋይላችን ላይ ወቅታዊ መረጃ ሊኖረን ይገባል፣ ለምሳሌ የፖስታ ሳጥን ቁጥር እና ስልክ ቁጥር(ሮች)።
- ሽፋናቸውን የተመለከቱ መረጃዎችን መከታተል እና በፍጥነት ምላሽ መስጠት።
- በኢሜይል እና በአጭር ጽሁፍ ለሚላኩ መረጃዎች ይመዝገቡ፣ coverva.org እና facebook.com/coverva/ ላይ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ይከተሉን

## ሌሎች የጤና ክብካቤ ሽፋን አማራጮች ምንድን ናቸው?

ለቨርጂኒያ Medicaid መስፈርቱን የማያሟሉ የቨርጂኒያ ነዋሪዎች በEnroll Virginia አማካኝነት የጤና መድን መግዛት ይችላሉ። Enroll Virginia የቨርጂኒያ ነዋሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው፣ አቅምን ያገናዘቡ የጤና ሽፋኖችን እንዲያገኙ ለመርዳት በመላው ግዛት ቢሮዎች አሉት። በFederal Marketplace ላይ HealthCare.gov ላይ ለመድን መመዝገብ ይችላሉ፡-

- የጤና ሽፋንዎን ባጡ በ60 ቀናት ውስጥ ወይም
- ከኖቬምበር 1 እስከ ዲሴምበር 15 ክፍት በሆኑ ማናቸውም ዓመታዊ የምዝገባ ክፍለ ጊዜዎች ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ።

ከMedicaid የጤና ሽፋን ለማግኘት መስፈርቱን የሚያሟሉ ወይም የማያሟሉ የቨርጂኒያ ነዋሪዎች በHealthCare.govአማካይነት የግል የጤና መድን ወጪን ዝቅ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይችሉ ይሆናል። የገንዘብ ድጋፉ መጠን አመልካቹ በሚኖርበት አካባቢ ባለው የመድን ወጪ፣ በቤተሰቡ አባላት ቁጥር፣ እና በግምታዊ ዓመታዊ ገቢያቸው ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

የበለጠ ለመረዳት enrollva.org ይመልከቱ ወይም በስልክ ቁጥር 888-392-5132 ይደውሉ፡-

- ለጤና መድን ሽፋን በመስመር ላይ ወይም በአካል በመገኘት ለመመዝገብ፣ አሳሾች ከትሰኙ የሰለጡኑ ረዳቶች እገዛ ያግኙ።
- ማንነትን በማያሳውቅ ለአጠቃቀም ቀላል በሆነ የመስመር ላይ መሳሪያ ዕቅዶችን እና ወጪዎችን ያወዳድሩ።
- ምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ ለመቀበል መስፈርቱን እደሚያሟሉ ይወቁ።
- ይመዝገቡ!!




## የበለጠ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የቨርጂኒያ Medicaid ለአባላቱ በ coverva.org፣ commonhelp.virginia.gov፣ ኢሜይሎች፣ በአጭር ጽሁፎች እና ማኅበራዊ ሚዲያ አማካይነት ወቅታዊ መረጃ ያደርሳል።

## ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ወይም ሃሳቤን ለማቅረብ ወደ የት መሄድ እችላለሁ?

አባላት በኢሜይል አድራሻ covervirginia@dmas.virginia.govሊያገኙን ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ Cover Virginia ድር ጣቢያን ይጎብኙ ።